Michigan.gov/VOTE

# 2024 የሚሺጋን (Michigan) ድምጽ ሰጪ መረጃ በ አማርኛ

## ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ

የሚከተሉትን ከሆኑ በሚሺጋን ውስጥ ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ ይችላሉ፡-

የአሜሪካ ዜጋ

- ቢያንስ ለ30 ቀናት የሚሺጋን (Michigan) ነዋሪ
- 17.5 ዓመት የሆነው እና 18 ዓመት የሆናቸው በምርጫው ቀን መምረጥ ይችላሉ (16 ዓመት እና 17 ዓመት የሆናቸው ደግሞ ድምጽ ለመስጠት አስቀድሞ መመዝገብ አለባቸው)
- በአሁኑ ጊዜ በእስር ቤት ወይም በወህኒ ቤት ውስጥ ቅጣት ላይ ያልሆነ

በኢንተርኔት መስመር ላይ Michigan.gov/Vote ላይ ይመዝገቡ ወይም የተተረጎመውን የድምጽ ሰጪ መመዝገቢያ ቅጽ Michigan.gov/SOSLanguageForms ላይ ፕሪንት ያድርጉ።

## ድምጽ በራስዎ መንገድ ይስጡ፡- በሚሺጋን (Michigan) ውስጥ ድምጽ ለመስጠት የእርስዎ አማራጮች

- በኢሜይል ድምጽ መስጠት፡- በምርጫ ላይ ለማይገኙ የድምጽ መስጫ ወረቀት መጠየቅ ቀላል እና አመቺ የድምጽ መስጫ መንገድ እንዲሆንልዎ በፖስታ ወደ ቤትዎ ይላክልዎታል። በኢንተርኔት መስመር ላይ የድምጽ መስጫ ቀን ለማይገኙ ለማመልከት በ Michigan.gov/Vote ያመልክቱ ወይም የተተረጎመውን ማመልከቻ ከ Michigan.gov/SOSLanguageForms ላይ ያውርዱ።

- ቀደም ብሎ በአካል በመገኘት ድምጽ መስጠት፡- ቀደም ብለው እና በአካል ተገኝተው በአቅራቢያዎ ድምጽ ለመስጠት ቀደም ተብሎ ድምጽ የሚሰጥበትን ቦታ ይጎብኙ። ኖቬምቤር ላይ ለሚደረገው ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት በአገር አቀፍ ደረጃ ከኦክቶበር 26 ጀምሮ እስከ ኖቬምቤር 3 ድረስ ይካሄዳል።

- በምርጫው ቀን ድምጽ መስጠት፡- በምርጫው ቀን የድምጽ መስጫ ወረቀትዎን ለማስገባት በአቅራቢያዎ ያለውን የድምጽ መስጫ ቦታ ይጎብኙ።

## የእርስዎ የድምጽ መስጠት መብቶች ሚሺጋን (Michigan) ውስጥ

- በድምጽ መስጫ ቦታዎች ላይ የትርጉም አገልግሎት፡- ድምጽ በሚሰጡበት ጊዜ እርስዎን እንዲረዳዎት አስተርጓሚ ይዘው ለመምጣት መብት አለዎት። የእርስዎ አስተርጓሚ የእርስዎ ድምጽ መስጠት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር፣ የእርስዎ አሰሪ፣ የአሰሪዎ ወኪል፣ ወይም ባለሥልጣን ወይም የእርስዎ የሕብረት ሥራ ማኅበር ወኪል መሆን የለበትም።

- ምንም ዓይነት ፎቶ ያለው መታወቂያ አያስፈልግም፡- ፎቶ ያለው መታወቂያ ባይኖርዎትም ድምጽ መስጠት ይችላሉ።

- ተመላሽ ዜጎች፡- በሚሺጋን (Michigan) ውስጥ ባለፉት ጊዜያት በወንጀል የተፈረደባቸው ግለሰቦች፣ ምንም እንኳን በይቅርታ ወይም በአመክሮ ጊዜ ላይ ቢሆኑም ለመመዝገብ እና ድምጽ ለመስጠት ብቁ ናቸው።

## የምርጫ ከለላ እናበድምጽ ሰጪ ላይ አሉታዊ ጫና

በምርጫው ዕለት ወይም ከዚያ በፊት ምንም ዓይነት ከድምጽ መስጠት ጋር የተያያዙ ችግሮች ካጋጠሙዎት፣ ወይም ስለድምጽ መስጠት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ድጋፍ ለማግኘት የምርጫ ከለላ ነጻ መስመርን በሚከተለው ላይ ያግኙ፡-

- 866-OUR-VOTE (866-687-8683)

በሚሺጋን (Michigan) ውስጥ ድምጽ ስለመስጠት በይበልጥ ለማወቅ በአማርኛ Mi.gov/SOSLanguage ላይ ያግኙ ወይም የQR ኮዱን ይቃኙ።